# ስድስት ዓመታት

(ለሳሙኤል ዓለማየሁ)

ስድስት ዓመታት አለፉ፣
የበላይ ሕይወት ካከተመ፣ ከተዘጋ ምዕራፉ፣
ተስፋችን ከተቀጨ፣ ከተቆረጠ ዘርፉ ።
አቤት ባይ አልተገኘ፣ መልስ ሰጪ፣
ሳሙኤልን ወደ እኛ አምጪ፣
ስሙን ብንጠራ ብንደጋግመው፣
የገደል ማሚቶ መሆን ነው።
ብናየው ላንዴ ተሳክቶ ምኞታችን፣
ብንጠይቀው ስሜቱን የመጨረሻ ጉዞውን፣
የታየውን ሕልም ያማረውን፣
ምን ይሆን የሚለን፣
ስለ ሕይወቱ የማለቂያ ኑዛዜውን፣
ቢንግረንስ ቢያወያየን፣
መች ልንረዳው ልንደርስበት፣
እንደሱ አይሆንልን አናውቅበት።
ብንለምነው ሞትን፣
ብንማጸነው አጥብቀን፣
እናዘገየው ይሆን? አትውሰደብን ብንለው፣
አልጠገብነውም ገና ትንሽ ዓመታት፣
ስጠን ብንለው ለግሰን ወራት፣
ካልሆነም እንኳን ጥቂት ቀናት፣
ደቂቃ ሰዓታት፣
ዞር ይል ይሆን ወይ ሞት ከመጣበት?
ያልፋት ነበርን ያቺን ጠዋት?
ዓይኖቹ ሊዘጉ፣ ላይከፈቱ ዳግመኛ፣

ሁሉን አሸናፊ አያ ሞት ሀይለኛ፣
የማይመርጥ የማያዳላ ጉልበተኛ ።
የዛሬ ስድስት ዓመት ሰማዩ ጠቆረ፣
ተድላችን ጠፋ ሳሙኤልም ቀረ፤ አመረረ ።

(ቀን ተሌት የሚናፍቁት ቤተሰቦቹ፣ 2004 ዓ. ም.)